የሰበር መ/ቁ. 23048

መጋቢት 27/1998

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጐስ ወልዱ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ ቀነብሽ ኪዳኔ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፍትፍት ብዙነህ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የጀመረው በሰ/ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ ከአባቴ በውርስ ማግኘት የሚገባኝን የውርስ ንብረት ያላግባብ ስለያዙብኝ ያስረክቡኝ በማለት በአመልካች በቀረበው ክስ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የአመልካች አባት ሟች አቶ ኪዳኔ ካሣ ታህሣስ 8/1988 ያተረፉት ኑዛዜ በፍ/ቤት ቀርቦ ስለፀደቀና አመልካችም የኑዛዜው ተጠቃሚ በመሆናቸው በኑዛዜው ላይ ከተሠጣቸው ስጦታ በቀር ሌላ ንብረት ሊጠይቁ አይችሉም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በዚህ ጉዳይ የቀረበለትን ይግባኝ ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሠበር ችሎት ባቀረቡት አቤቱታም ፍ/ቤቱ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው ኑዛዜ ቀደም ሲል ፍ/ቤት እንዲፀድቅ ቀርቦ ውድቅ የተደረገ በመሆኑ ይህንን ኑዛዜ መሠረት በማድረግ ውሣኔ መሠጠቱ የሕግ ስህተት በመሆኑ ውሣኔው እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 15/9/98

ይህ የሠበር ችሎትም ቀደም ሲል ተጠሪ የኑዛዜ ወራሽነታቸው እንዲረጋገጥላቸው ባቀረቡት አቤቱታ ኑዛዜው ውድቅ ከተደረገ በኂላ ይህን የኑዛዜ ሠነድ መሠረት በማድረግ ውሣኔ መሠጠቱ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመመርመር ጉዳዩን ለሠበር በማስቀረብ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል።

ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ክስ የመሠረቱት የወላጅ አባታቸውን የአቶ ኪዳኔ ካሣን ንብረት ተጠሪ ይዘው የአመልካችን ድርሻ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የአመልካችን ድርሻ እንዲያካፍሉ ነው። ተጠሪ በበኩላቸው ሟች ኑዛዜ የተው በመሆኑ አመልካች በዚህ ኑዛዜ የተሠጣቸውን ብር 300 /ሦስት መቶ/ ከመጠየቅ በቀር ሌላ ንብረት ሊጠይቁ አይችሉም ሲሉ ተከራክረዋል ፍ/ቤቱም የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ሟች ታህሣስ 8/1988 ያደረጉት ኑዛዜ ፍ/ቤት ቀርቦ ፀድቋል፣ በዚህ ኑዛዜ ለአመልካች ብር 300 /ሦስት መቶ/ ተሠጥቷል፣ ስለሆነም አመልካች በኑዛዜው ከሚጠቀሙ በቀር ሌላ ንብረት ሊጠይቁ አይችሉም በሚል ምክንያት ነው።

ይሁን እንጂ ይህ ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ተጠሪ በጎንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሚስትነታቸውና የኑዛዜ ወራሽነታቸው እንዲረጋገጥላቸው ኑዛዜውን በማያያዝ አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 173/91 ኑዛዜውን ውድቅ ማድረጉን አመልካች አጥብቀው ተከራክረዋል። ይህ ችሎትም የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 173/91 በሠጠው ውሣኔ ላይ ለጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቀርቦ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን ተመልክቷል። በዚህም ውሣኔ ተጠሪ ሟች ታህሣስ 4 ቀን 1988 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሠጣቸው ያቀረቡትን ጥያቄ የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ተመልክቶ በ22/03/93 ውድቅ ያደረገው መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህን የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔም የከፍተኛ ፍ/ቤቱ አልሻረውም። በመሆኑም የወረዳ ፍ/ቤቱ በ22/03/93 በዋለው ችሎት ኑዛዜው ህጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 15/9/98

የሠጠው ውሣኔ አልተሻረም ወይም ስለመሻሩ ተጠሪ ያረጋገጡት ፍሬ ነገር የለም። ይልቁንም ተጠሪ ይኸው ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው አዲስ መዝገብ ቁጥር 124/93 የሆነ አስከፍተው ኑዛዜው ሰኔ 20/1993 ዓ.ም. እንዲፀድቅላቸው ማድረጋቸውን ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል። ቀድሞ ፍርድ ከተሠጠው ክርክር ሥረ-ነገር እና ጭብጥ አንድ አይነት በሆነ ጉዳይ ላይ ለ2ኛ ጊዜ ክስ ወይም አቤቱታ ሊቀርብ እንደማይቻል ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5 መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ተጠሪ ቀደም ሲል ሕጋዊ ውጤት የለውም የተባለው የኑዛዜ ሰነድ ለፍ/ቤት በማቅረብ እንዲፀድቅላቸው አዲስ አቤቱታ ማቅረባቸው ከላይ የተመለከተውን የሕግ ድንጋጌ የሚጥስ በመሆኑና የሥር ፍ/ቤቶችም በዚህ መልኩ ፀድቆ የቀረበውን የኑዛዜ ሠነድ መሠረት በማድረግ አመልካች በኑዛዜው መሠረት ከሚጠቀሙ በቀር የአባታቸውን ሌላ ንብረት ሊጠይቁ አይችሉም በማለት በሠጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል።

## ው ሣ ኔ

1. የሰ/ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02437 ጥር 27/1997 እና የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05848 ታህሣስ 24/1998 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል።
2. የሰ/ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የኑዛዜ ሰነዱን ብቻ መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሣኔ የተሻረ በመሆኑ አመልካች የአባታቸውን ንብረት በድርሻቸው ለመካፈል ያቀረቡትን ጥያቄ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩ ለከፍተኛ ፍ/ቤቱ ተመልሷል።
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ።

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ——— ቀን 15/9/98